የሰ/መ/ቁ. 213747

ቀን ፡- ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ኤምቲጂዲ ኤሌክትሮ ሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር --ጠበቃ ዳንኤል ግርማ

ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ኮንሳልት ኮንሶራዚኦ አልታቴንሲዮኔ ኢትዮጵያ ብራንች

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ።

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ

የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው። የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ

እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ፤ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል። አመልካች ያቀረበው

ክስ ውልን መሠረት በማድረግ ተጠሪ ብር 10,386,376.43 እንዲከፍለው ዳኝነት ጠይቋል። ተጠሪ ባቀረበው

መከራከሪያ በውላችን መሠረት አለመግባባት ቢከሰት በግልግል ጉባዔ እንዲታይ የተስማማን በመሆኑ ፍርድ

ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ክሱ እንዲሰረዝ ጠይቋል። የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ጉዳዩን መርምሮ በውላቸው አንቀጽ 17 መሠረት አለመግባባት ሲኖር በዓለምአቀፍ የንግድ ምክር ቤት

የግልግል ተቋም እንዲታይ የተስማሙ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት

ወስኗል። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ ተቀብሎ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ

ችሎት

በማከራከር በውሉ አንቀጽ 17 ላይ አለመግባባት ቢከሰት ተዋዋይ ወገኖች በመጀመሪያ ደረጃ ለመወያየትና

ጉዳዩን በአይሲሲ የአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎች ሕጎች መሠረት መፍትሔ ለመስጠት መስማማታቸውንና፤ ክርክሮች በመጨረሻም በዓለምቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም ድንጋጌዎች መሠረት በአንድ ወይም ከአንድ በላይ ገላጋይ ዳኛ አማካኝነት እልባት የሚያገኝ ስለመሆኑ ተመልክቷል። በሥምምነት ለመጨረስ አመልካች ጠይቆ ያልተሳካ በመሆኑ ጉዳዩ በግልግል ጉባዔ የሚታይ ነው። ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት ውሳኔውን አጽንቷል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የውሉ አንቀጽ 17 ፡- ከዚህ ሥምምነት ጋር በተያያዘ አለመግባባት ከተከሰተ ተዋዋይ ወገኖች በመጀመሪያ ውይይት ለማድረግ ጉዳዩ በአይሲሲ ኤዲአር ሕግጋት መሠረት ለግልግል ሂደት ማቅረብን እንደ አማራጭ ለመውሰድ ተስማምተዋል ይላል። ይሕም ተዋዋዮች ከፈለጉ እንደአማራጭ የሚጠቀሙት፤ ካልፈለጉ ደግሞ የሚተውት ሆኖ ሥምምነቱ መደረጉን ያሳያል። መተርጎም ያለበት የአንቀጽ 17 የመጀመሪያ ዓረፍተ ነገር ነው፤ ዓረፍተ-ነገሩ ግልጽ ነው፤ ግልጽ አይደለም ከተባለም መተርጎም ያለበት መብቱን የሚያጣው ወይም የሚገደደው ተዋዋይ ወገንን በሚደግፍ መልኩ ነው። ተጠሪ የትኛውን አማራጭ እንደሚደግፍ ደብዳቤ ተጽፎለት ምላሽ ያልሰጠ በመሆኑ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ ይገባል የሚል ነው። የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ፍርድ ቤቱ ክሱን ለማየት ሥልጣን የለኝም ማለቱ ከውሉ አንቀጽ 17 አኳያ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረበው መልስ በውሉ አንቀጽ 17 አማራጭ ሆኖ የተቀመጠ አይሲሲ ኤዲአር (ICC ADR) ሕግጋት ግጭት መፍቻ መንገዶች ተብለው የተቀመጡት እርቅና ሥምምነት ናቸው። ወደግልግል መሄድ አለመሄድ አማራጭ ሆኖ በውሉ አልተመለከተም። ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በሏል። አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካች ያቀረበው ክስ በግልግል ጉባዔ የሚታይ ነው ተብሎ መወሰኑ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን? በጥብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል። እንደመረመርነው አመልካች በውል መሠረት ያልተከፈለ ገንዘብና የደረሰ ኪሣራ ተጠሪ እንዲከፍለው ክስ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የውል አለመግባባት ሲኖር በግልግል ጉባዔ ለመዳኘት ስለተስማማን ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይ አይገባም በማለት ተከራክሯል። የዳኝነት ሥልጣን በመርሕ ደረጃ የሚወሰነው በሕግ ቢሆንም ተዋዋዮች በሕግ በተፈቀደው አግባብ አለመግባባት የሚታይበትን የዳኝነት አካል የመምረጥ መብት አላቸው። ሰዎች በመካከላቸዉ ከፈጠሩት ሕጋዊ ተግባራት በመነጨ ወይም ከዚህ ጋር በተያያዘ ለወደፊት

በመካከላቸዉ የሚፈጠረዉን አለመግባባት ወይም ተፈጥሮ ያለዉን አለመግባባት ከመደበኛ ፍርድ ቤት ዉጭ

በግልግል ዳኝነት በኩል ለመፍታት የመዋዋል ነጻነታቸዉን በመጠቀም መስማማት እንደሚችሉ የፍ/ሕ/ቁ.

3328 እና የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315(1) ያስረዳሉ። የግልግል ዳኝነት ሥምምነት በጽሁፍ በተዋዋሉት በዋናዉ

ዉላቸዉ በሚያደርጉት የግልግል ዳኝነት ስምምነት ቃል (Arbitration Clause) ወይም አስቀድሞ

በመካከላቸዉ ተከስቶ ያለዉን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት ለመፍታት ራሱን በቻለ የጽሁፍ የግልግል

ዳኝነት ስምምነት (Arbitral Submission) ሊመለከት ይቻላል።

ተዋዋዮች በውል አለመግባባቱ የሚታይበትን ሥርዓት ከወሰኑ ውል በፍ/ሕ/ቁ. 1731(1) እንደተመለከተው

በተዋዋዮች መካከል እንደ ሕግ አስገዳጅ በመሆኑ በወሰኑት የዳኝነት አካል የመዳኘት ግዴታ ይጥልባቸዋል።

በግልግል ዳኝነት ሊታይ የሚገባው ክስ ፍርድ ቤት ከቀረበ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለሌው

ስለመሆኑ ውላቸውን መሠረት በማድረግ ተከራካሪዎች ወይም ፍርድ ቤቱም በግልግል እንዲታይ ሥምምነት

መኖሩን ካወቀ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9(2) መሠረት በማናቸውም የክርክሩ ደረጃ ሊያነሳው ይችላል። ፍርድ

ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የማይኖረው በሕግ መሠረት ይሁን በተዋዋዮች የግልግል ዳኝነት ጉባዔን

መምረጥ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው። ጉዳዮች ከፍርድ ቤት ውጭ እንዲታዩ ካስፈለገበት ዓላማ አንዱ የፍርድ

ሂደት ቅልጥፍና (efficiency) ለመጨመር በመሆኑ ተዋዋዮች ጉዳዩ በግልግል ጉባዔ እንዲታይ ከተስማሙ

በኋላ ሊተው እንደሚችል መብት (waivable right) ተቆጥሮ ክሱን በፍርድ ቤት ካቀረቡት ለግልግል ጉባዔ

የማቅረብ መብታቸውን እንደተውት የሚቆጠርና ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን የሚሰጠው

አይደለም። ሥለሆነም በውል ያላቸውን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት እንዲታይ ያደረጉትን ሥምምምነት

በተመሳሳይ የጽሁፍ ሥምምነት አድርገው እስካላሻሻሉት ድረስ የዳኝነት ሥልጣን በተከራካሪዎች የክርክር

አቀራረብ ሆነ ክርክሩ በደረሰበት ደረጃ ምክንያት የሚወሰን አይደለም።

በተያዘው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት የውል ሥምምነት አንቀጽ 17 ላይ "In the event of any

dispute arising out of or in connection with this agreement, the parties agree in the first

instance to discuss and consider submitting the matter to settlement proceedings under ICC

ADR Rules. Disputes shall be finally settled under the rules of arbitration of the international

chamber of commerce by one or more arbitrators appointed in accordance with the said

rules of arbitration” ተብሎ ተመልክቷል። አንቀጽ 17 አለመግባባት ቢከሰት ተዋዋይ ወገኖች በመጀመሪያ ደረጃ ለመወያየትና ጉዳዩን በዓለምአቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም የአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎች ሕጎች መሠረት መፍትሔ ለመስጠት መስማማታቸውንና፤ ክርክሮች በመጨረሻም በዓለምቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም ድንጋጌዎች መሠረት በአንድ ወይም ከአንድ በላይ ገላጋይ ዳኛ አማካኝነት እልባት የሚያገኝ ስለመሆኑ መስማማታቸውን ያረጋግጧል።

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በውሉ ድንጋጌ የመጀመሪያ ዓረፍተ-ነገር መሠረት ወደ ግልግል ጉባዔ መሄድ አለመሄድ በተዋዋዮች ምርጫ የሚወሰን ስለመሆኑ ያመላክታል በማለት ነው። የውሉ አንቀጽ 17 ሁለቱም ዓረፍተ-ነገሮች በዓለምአቀፍ የንግድ ምክር ቤት አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ሕግጋትን የሚገልጹ ናቸው። የግራቀኙ የውል ሥምምነት የመጀመሪያ ዓረፍተ-ነገር እንደሚያስገነዝበው ተዋዋዮች በመወያየትና በመነጋጋር አለመግባባታቸውን በዓለምአቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም የአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎች ሕጎች መሠረት መፍትሔ ለመስጠት መስማማታቸውን የሚገልጽ ሲሆን ቀጥሎ ያለው የውሉ አካል በመጨረሻም በዚሁ ተቋም ጉዳዩ በግልግል የሚያልቅ መሆኑ መመላከቱ ሲታይ የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር በዓለምአቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም ከግልግል ውጭ ያለ አለመግባባት የሚፈታበት ዘዴን የሚመለከት ስለመሆኑ ተረድተናል። የዓለምአቀፍ የግልግል ተቋም አለመግባባትን በግልግል የመፍታት ዘዴ ደንቦች (arbitration rules) እና አለመግባባትን በእርቅና በሥምምነት የመፍታት ዘዴ ደንቦች (mediation rules) ያካተተ ነው። አመልካችና ተጠሪ ጉዳያቸውን በዓለምቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም በእርቅና በሥምምነት ለመጨረስ መወያየት የሚችሉ ስለመሆኑ የተመለከተ ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት እንደተረጋገጠው በዚህ አግባብ ለመፍታት ስላልተስማሙ ጉዳዩ በግልግል የሚታይና የመጨረሻ እልባት በዓለምቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም አማካኝነት የሚሰጠው እንጂ ክሱ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የለንም በማለት የአመልካችን ክስ መሰረዛቸው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም።

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 196236 ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 252488 ሐምሌ 28 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል።

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ።
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት